አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ቀን የካቲት ፲፫/ ፪ሺ፯ ዓ/ም

Date: 04/21/2015

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ። አሜን።

## በስደት በሊቢያ ሳሉ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በሰማዕትነት ስላረፉት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከሚመራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ

«እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።» ራዕይ 7፥14፡15።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያውያን በችግር ምክንያት ቀን ከብዶባቸውና ተቸግሮ መኖር ሰልችቷቸው ባህሩንና ገደሉን እያቋረጡ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በመሰደድ ላይ ይገኛሉ። ኢትዮጵያውያን በሄዱበት ሠርተው ራሳቸውን ረድተው መኖር የሚፈልጉ ሰላማውያን ሕዝቦች ናቸው። ቀን ጥሏቸው ይሰደዱ እንጅ አንግዳ ማስተናገድ የሚያውቁ ሕዝቦች ናቸው። በእንግድነት ወደነሱ የሚሄደውን ማንኛውንም ሰው አክብረው የሚቀበሉ፤ የሚበሉትን አብልተው፣ የሚጠጡትን አጠጥተው የሚያስተናግዱ፣ ለሰው ልጅ ማንነት ክብር የሚሰጥ ባሕል ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። ይሁን እንጅ በእንግድነት ወደ ባእድ ሀገር ሲሰደዱ ሲያጋጥማቸው የምናየው መከበርን ሳይሆን መናቅን፣ ተቀባይነትን ሳይሆን መገፋትን መሆኑን በተደጋጋሚ በወገኖቻችን ላይ የሚደርሱ ኢሰብአዊ በደሎች ምስክሮች ናቸው። በባእድ ሀገር በአረመኔዎች በፎቅ ላይ ይወረወራሉ፤ በእሳት ያቃጥሏቸዋል፣ ወደ ባህር ይጥሏቸዋል፣ አሁን ደግሞ በሊቢያ እንደሚታየው ኢትዮጵያውያንን ክርስቲያኖች በመሆናቸው ብቻ በስለት አርደዋቸዋል፣ በጥይት ደብድበዋቸዋል።

የሚያሳዝነው ግን ሕዝባችን በሀገሩ ላይ በፍጹም ነጻነትና ክብር፣ እንዲሁም በእኩልነት መብቱ ተከብሮለት መኖር ባለመቻሉና ድኅነትም ስለሚያስጨንቀው ይህ ሁሉ መከራ በባዕድ ሀገር መኖሩን እያወቀ፣ የሆነ ይሁን ብሎ ስደቱን አልተወውም። ይህም ሕዝባችን በሀገሩ ምን ያክል ቢከፋው ነው? እንዴትስ ችግር ቢያጠቃው ነው? መፍትሔውስ ምንድን ነው? ብለን እንድናስብ ያስገድደናል። ኢትዮጵያ ሀገራችንን ሀገር አድርገን፣ ሕዝባችን በነጻነትና በክብር በሀገሩ ተከብሮ እንዲኖር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልዩነትን ትቶ በፍቅርና በአንድነት ለሀገሩ ሰላም፣ አንድነትና እድገት መሥራት እንዳለበት በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለው መከራ ሊያነሣሳው ይገባል።

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031

ስደቱ የብዙ ኢትዮጵያውያን እድል ፈንታ ቢሆንም ለክርስቲያኖች ደግሞ ትልቅ የፈተናና የስቃይ ምዕራፍ ሁኗል። ምክንያቱም ክርስቲያኖችን መግደልና ማሰደድን እንደ ጽድቅ ሥራ የሚቆጥረውና እስላማዊ መንግሥትን እመሠርታለሁ የሚለው ነፍሰ ገዳይ አካል በዓለም ዙሪያ ክርስቲያኖችን በመግደልና ባማሳደድ ላይ በመሆኑ ነው። ቀደም ሲል በመካከለኛው ምስራቅ ማለትም በሦርያና በኢራቅ፤እንዲሁም በአፍሪካም በሊቢያ በሚኖሩ የግብጽ ክርስቲያኖች፣ በኬንያ ክርስቲያን ተማሪዎች ላይ የተፈጸመው ግፍ የትናት ታሪክ ነው። እራሳቸውን የእስላም እምነት አራማጆች አድርገው በሚንቀሳቀሱ ነፍሰ ገዳዮች የብዙ ክርስቲያኖች ደም በግፍ ፈሷል። አሁንም በመፍሰስ ላይ ነው፤ ብዙዎች ክርስቲያኖችም በእስር ቤት ይገኛሉ፤ እንደ ሰው በሀገራቸው በነፃነት የመኖር መብትም የላቸውም።

አሁን ደግሞ በመላው ዓለም በሽብር ሥራው ንጹሐን ክርስቲያኖችን ደም በማፍሰስ ላይ ያለው እና « እስላማዊ መንግሥት»( አይሲስ) በማለት ራሱን የሚጠራው ይህ ሃይማኖት የለሽ የሽብር ቡድን፥ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ/ም በጭካኔ መግደሉ ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ ቅዱስ ሲኖዶስ በታላቅ ሐዘን ላይ ነው። በሰው አምሳል ተፈጥረው ከአራዊት የከፋ ሥራ የሚሠሩ የአረመኔዎችን ሥራ ቅዱስ ሲኖዶስ ያወግዘዋል።

እነዚህ ንጹሐን ወገኖቻችን ለዚህ ሰማዕትነት የበቁትም ክርስቲያኖች በመሆናቸውና ክርስትናቸውን ሳይክዱ እስከመጨረሻ እስትንፋሳቸው በእምነት በመቆማቸው ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ስለ እነዚህ ሰማዕታት ለፈጣሪዋ ምስጋና ታቀርባለች። የእነዚህ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት ደምም የክርስትና ዘር ስለሆነ ፥ በመላው ዓለም ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ከመቼው ጊዜ በበለጠ፥ በምስጋና በጸሎት በእምነት ጸንተው፥ የክርስትናቸውን ጽናት ለዓለም ያውጃሉ።

የእነዚህ ንጹሐን ሰማዕታት ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ስለሆነ መራር የሆነው አሟሟታቸው በከፍተኛ ሐዘን ላይ ቢጥለንም፥ በአምላካቸው ዘንድ የተዘጋጀላቸውን ሰማያዊ አክሊል ስናስብ ደግሞ ታላቅ መንፈሳዊ ደስታ ስለሚሰማን፥ ዕረፍታቸውን የምናስበው በታላቅ የሃይማኖት መንፈስ እና በምስጋና ነው። ይህ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ ነገር አይደለም፣ በደም ቀለም የተጻፈው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አካል ስለሆነ። ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ የሰጠላት ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ስለእርሱ ራሷን አሳልፋ ስትሰጥ ነው የኖረችው። ዘመነ ሰማዕታት በዘመናችን ተመልሶ እየመጣ መሆኑን ሳይበድሉ ስለ ክርስቶስ ስም በአረማውያን ፊት በእምነት ቁመው ከአረማውያን ሰይፍና ጠብመንጃ ይልቅ ክርስቶስን የፈሩት ክርስቲያኖች ንጹህ ደም ምስክር ነው።

በመጨረሻም ፡-

1ኛሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከአበው የተቀበለውን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሰረት በማድረግ ለእነዚህ በሃይማኖት እስከሞት ድረስ የታመኑ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ክብር የሚሰጥበትን መንገድ ቅዱስ ሲኖዶስ እስከሚያዘጋጅ ድረስ ከዛሬ ጀምሮ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እስከሚከናወንበት እስከ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ድረስ በጸሎተ ፍትሐትና በምህላ ሰማዕታቱን እንድታስቡ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል። እንዲሁም በየመን በስደት ሳሉ የጦርነት ሰለባ ለሆኑ፣በሜድትራኒያን ባሕር ለሰጠሙት፣ በደቡብ አፍሪካ ለሞቱትና ለሚንገላቱት፣ በሊቢያ የድረሱልን ጥሪ ለሚያሰሙት ኢትዮጵያውያን እግዚአብሔር አምላክ መከራቸውን አይቶ በምሕረት እንዲያስብልን በጸሎት እንድናስባቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

2ኛ በግፍ ደማቸው የፈሰሰውን ኢትዮጵያውያን ቤተ ሰቦች በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንድንረዳቸው፣

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031

3ኛ በዚህ ዘመን ከምንም በላይ የሚያስፈልገን አንድነት ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ካዳቦ ይልቅ አንድነትን የተራበበት ዘመን ነው። እግዚአብሔርም የሚባርከን አንድ ልብ ሁነን ስንለምነው ነው፤ ስለዚህ በሀገራችን በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ ልዩነትን በማስወገድ በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ ሁናችሁ ለአገራቸሁና ለሕዝባችሁ እንድትሠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ! በዓለም የተበተነውን ሕዝባችንንም ይጠብቅ።

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031